# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት



## መጽሐፍ ቅዱስ እና ታሪኩ

*ፓ/ር መስፍን ማንደፍሮ*

**እንደ መነሻ**

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ጥያቄዎች ጠይቀን የምናገኘው ምላሽ ሊያስገርመን ወይም ሊያስፈግገን ይችላል። ለምሳሌ ከተማ ተወልደው ያደጉ ልጆችን “ወተት የሚገኘው ከየት ነው?” ብለን ብንጠይቃቸውና “ወተትማ የሚገኘው ከሱቅ ነው፤” ብለው ቢመልሱ በአግራሞት ፈገግ ሊያሰኘን ይችላል። መልሳቸው ግን እውነታ አለበት ምክንያቱም ለነዚህ ልጆች ላም ያሳያቸው ስለሌለ የወተትን መገኛ የሆነችውን እንስሳ እንዲዘነጉ አድርጓቸዋል። ሆኖም በእነዚህ ልጆች ምላሽ ልንፈርድ አንችልም፤ ምክንያቱም ካልተማሩ ሊያውቁ አይችሉም።

በተመሳሳይ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ ከየት መጣ? ከሰማይ ወረደ? የስሙስ ትርጉም ምን ማለት ነው? መጀመሪያ የተጻፈው በምን ላይ ነው? በወረቀት? በቅጠል? በቆዳ? የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ዛሬ የት ይገኛሉ? ከዘመን ዘመን እጅግ በርካታ ዓመታትን አልፎ እንዴት በዚህ ዘመን በእጃችን ላይ ለመገኘት ቻለ? በምን ቋንቋስ ተጻፈ? ከጥፋትስ እንዴት ተጠበቀ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት 66ቱ መጻህፍትስ እንዴት ተሰባሰቡ? ወዘተ ተብለን ብንጠየቅ መልሳችን ምን ይሆናል? እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች በዚህ መሰሉ መጣጥፍ በብቃት ለመመለስ አስቸጋሪ ቢሆንም ካሁን ጀምሮ በምናቀርበው ተከታታይ ጽሁፍ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት እንሞክራለን።

ባለንበት ዘመን በኮምፒውተር ወይም በስልካችን ላይ በቀላሉ ጠቆም በማድረግ በፍጥነት ከፊት አድርገን የምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ ከጥንት ከአፈጣጠሩ ወይም ከአዘገጃጀቱ ብዙ የሚገርሙ ሂደቶችን ያለፈ ነበር። የመጀመሪያዎቹ ጽሑፎች በፓፒረስ (ከደንገል በተሠራ ወረቀት) ከዚያም በብራና ላይ የተፃፉ ሲሆን ይህም የወረቀት መገኘት ከቻይና ወደ መካከለኛው ምስራቅ እስከመጣበት መካከለኛው ዘመን ድረስ የቀጠለ ልምድ ሆኖ እናገኘዋለን።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ቀደም ባሉት ዘመናት መልዕክትን በጽሑፍ ማስተላለፍ ከመጀመሩ በፊት መልዕክቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት በቃል ወይም በንግግር ነበር። ይህ የግንኙነት መንገድ ምንም ያህል ጥንቃቄ ቢደረግበትም መልዕክቱ ከሰው ሰው እየተላለፈ ሲሄድና ዘመናት ሲቆጠሩ የመጀመሪያው የቃል (የንግግር) ይዘት ለመቀየርና ለመዛባት የተጋለጠ ነበር። ይህንን ለማረጋገጥ ያለ ቤተሙከራ ምርምር ሰዎች በተሰባሰቡበት ቦታ አንድን ዘገባ በቃል (በንግግር) በማስተላለፍ ብዙም ሳይቆይ እንዴት ተለውጦና ተጣምሞ የመጨረሻው ሰው ዘንድ እንደሚደርስ ለማወቅ ብዙዎቻችን የሚያዳግተን አይደለም። ደቀመዛሙርት እንኳን ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን ቃል በደንብ ሳያዳምጡ፤ የተናገረውን በስህተት አስተውለው ስህተተኛ መልዕክት እንዳስተላለፉ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ቁጥር 23 ላይ ተጽፎ እናገኛለን። በዚህም ምክንያት በአፈታሪክ ወይም በቃል የሚተላለፍ መልዕክትን ለማመን አስቸጋሪ ሆኖ እናገኘዋለን። በተቃራኒው በጽሑፍ የሚተላለፍ መልዕክት ግን እንደ ቃል መልዕክት የመዛባት ችግር ሳይገጥመው የተፈለገበት ቦታ የመድረስ ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ሳይጣመም በትክክል የመድረስ አቅም አለው፤ ደግሞ ደጋግሞም በተላለፈ ቁጥር ሳይዛባና ሳይበረዝ ወጥነቱን ጠብቆ በመተላለፍ ረገድ ከአፈታሪክ ይልቅ በእጅጉ የበለጠና የተሻለ ነው።

በእርግጥ እግዚአብሔር መልዕክቱን በመላዕክት ሊነግረን ይችል ነበር፤ ለነብያቱም እንደሚናገረው በራዕይና በህልም፣ በድምጽና ተዓምራዊ በሆኑ መንገዶች ሊገልጽልን ይችላል። እነዚህን መንገዶችን ግን አልተጠቀመም። ከዚህ ሁሉ ይልቅ በላቀ ሁኔታ በጽሑፍ የሚተላለፍ መልዕክት ግልጽና ያልተዛባ በመሆኑ ተዓማኒነቱን የበለጠ ከፍ ስለሚያደርገው ይህንን መንገድ ነው የተጠቀመው። ይህም ዘዴ መልዕክትን ለትውልድ አቆይቶ ለማስተላለፍ ከሁሉ የበለጠ ተመራጭ አድርጎታል።

መጽሐፍ ቅዱሳችን በዕብራውያን 1፡1 ላይ እግዚአብሔር “በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና” ከጥንት ጀምሮ ሲናገር እንደነበር ያስረዳል። እንግዲህ ከአዳም እስከ ሙሴ በነበረው ዘመን መልዕክት በአብዛኛው በቃል ይተላለፍ የነበረበት ሲሆን ሃሳብን በጽሑፍ ማስተላለፍ ከተቻለ በኋላ ግን ሙሴ (1400 ከልደት በፊት ወይም ዓ.ዓ.) ከእግዚአብሔር የተላከልንን መልዕክት ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሁፍ ያስተላለፈ ሰው ሆኖ እናገኘዋለን።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

**መጽሐፍ ቅዱስ ስሙን ከየት አገኘ?**

ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ስሙን ያገኘው ከየት ነው? በአማርኛ “መጽሐፍ ቅዱስ” በእንግሊዘኛ “ሆሊ ባይብል” (Holy Bible) የሚለው ስያሜ እንዴት እንደተሰጠ ለማወቅ ብዙም የሚያስቸግር አይደለም። በተለይ የእንግሊዝኛው “ባይብል” የሚለው ቃል የመጣው ላቲንኛው ከግሪክ ከወሰደው “ቢብልዮን” (biblion) ከሚለው ቃል ነው። ስያሜውም በፓፒረስ (ከደንገል በተሠራ ወረቀት) ላይ ለተጻፉ ጥቅልል ጽሑፎች ከተሰጡ ስያሜዎች መካከል አንዱ ሲሆን ትርጉሙም “መጽሐፍ” ማለት ነው። ይህ ደግሞ በአማርኛ ለመጽሐፉ ከተሰጠው ስያሜ ጋር ይስማማል። ፓፒረስ በጥንት ዘመን ጽሑፍን ለመፃፊያ የሚያገለግል ጥቅል የሚዘጋጅበት በግብጽ አገር በናይል ወንዝ አካባቢ የሚገኝ ተክል ነው። እነዚህ የፓፒረስ ተክሎች ግንዳቸው ተፍቆ ከተዘጋጁ በኋላ ተቀጣጥለው በጥቅል መልክ ለጽሑፍ መፃፊያነት በተፈለገው ርዝመት ይዘጋጃሉ። ጽሑፍ ከተጻፈባቸው በኋላም አንባቢው በአንድ እጁ የጥቅልሉን እጀታ ይዞ በሌላው እጁ ደግሞ ጥቅሉን እየተረተረ ያነባቸዋል። ታዲያ በግሪክ እንደዚህ አይነት የጽሑፍ ጥቅል “ቢብልዮን” የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን ትርጉሙም ጥቅልል ጽሑፍ ወይም ጥቅል መጽሐፍ ማለት ነው።




ሰብዓ ሊቃናት ወይም “ሴፕቱአጀንት (Septuagint)” (250 ዓዓ) በመባል የሚታወቀው ከእብራይስጥ ወደ ግሪክኛ የተተረጎመው ብሉይ ኪዳን ውስጥ፤ በዳንኤል 9፡2 ላይ “እግዚአብሔር በቃሉ ለነቢዩ ለኤርምያስ የተናገረውን የዓመቱን ቍጥር **በመጽሐፍ** አስተዋልሁ” በሚለው ጥቅስ “በመጽሐፍ” በሚለው ቃል ፈንታ “ቢብሊያ” የሚለውን የግሪክ ቃል የተጠቀመበት ምክንያት ለዚህ ነው። ስለዚህ ግሪክ ተናጋሪ የነበሩት ክርስቲያኖች የአዲስና የብሉይ ኪዳን መፃህፍትን “ቢብሊያ” በማለት በመጥራታቸው ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ በእንግሊዝኛ “ባይብል” የሚለውን ስም እንዲይዝ አድርጎታል። ከዚህም ሌላ ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ይኖር የነበረ ክሊመንት የተባለ የሮም ቤተክርስቲያን ጳጳስ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ የአዲስ ኪዳን ጽሑፎችን “ቢብሊያ” በማለት እንደጠራቸው የታሪክ ድርሳናት ያረጋግጣሉ።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ቅዱሳችን ውስጥ “ቢብሊያ” ከሚለው አጠራር ውጪ ሌሎች ስያሜዎችንም እናገኛለን። ከነዚህም ውስጥ በተለይ ተመሳሳይነት ያላቸው ሁለት የግሪክ ቃላት አሉ። እነርሱም “ሐይ ግራፋይ - hai graphai” (ማቴዎስ 21፡42፣ ማርቆስ 14፡49፣ 2ኛ ጢሞቲዎስ 3፡16፣ 2ኛ ጴጥሮስ 3፡16ና ሮሜ 1፡22) እና “ታ-ሂራ ግራማታ - ta-hiera grammata” 2 ጢሞቲዎስ 3፡15 የሚባሉት ናቸው። እነዚህ ሁለት የግሪክ ቃላት “ጽሑፎችና ቅዱሳን ጽሑፎች” ተብለው በቅደም ተከተል ሊተረጐሙ ይችላሉ። ስለዚህ የአማርኛችንም “መጽሐፍ ቅዱስ” የሚለው ስያሜ ከዚህ እንደተገኘ መገመት አያስቸግርም።

**መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ዓላማ**

እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተዘግቦ የሚገኘው መገለጥ ስለ ፈጣሪ አምላካችን የበለጠ እውቀት እንዲኖረንና ሕጉንና ስርዓቱን ለመታዘዝ ትልቅ ኃላፊነት እንዲሰማን የሚደርግ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንደ ታላቅ ስነጽሑፍ ወይም የእስራኤልንና የቀደመችው ቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚዘግብ የታሪክ መጽሐፍ ወይም ስነ መለኮታዊ ይዘት እንዳለው ጽሑፍ ብቻ በመመልከት ልናነበው እንችል ይሆናል። ነገር ግን የተፃፈበት ዓላማ ከዚህ በላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ስለ እግዚአብሔር ሊገልጥልንና ሕይወታችንም ከእርሱ ጋር በሚኖረን ሕብረት እንዲለወጥ ለማድረግ ነው። 2ኛ ጢሞቲዎስ 3፡15-16 መጽሐፍቱ የተጻፉበትን ዓላማ በመዘርዘር እግዚአብሔርን በመታዘዝ እንድንኖር ያደፋፍረናል። ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ የተባሉትን የሰው ልጆችን ጥያቄ በበቂ ሁኔታ የመመለስ ታላቅ ዓላማ እንዳለው ለመገንዘብ እንችላለን።



ሥዕላዊ አጻጻፍ(Pictograms) ©Public Domain

ሰዎች ሃሳባቸውን በጽሑፍ መግለጽ ከመቻላቸው በፊት መረጃ የሚተላለፈው በቃል ወይም በንግግር እንደነበር ቀደም ብለን ጠቅሰናል። የሚተላለፈው መረጃ ትክክለኛነት በመልዕክት አቅራቢው የማስታወስ ችሎታ ላይ የሚወሰን ነበር። ነገር ግን ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ራሳቸውን በትክክል በጽሑፍ ለመግለጽ እንዲችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን ፈልስፈዋል፣ ለምሳሌ ስዕልን ተጠቅመዋል። አንዳንድ ድምጾችንና ሃሳቦችን ከተራ ስዕል ጠንከር ባሉ አገላለፆች ለማስረዳት ሲሉ ሥዕላዊ አጻጻፍን (Pictograms) እና እንደ

ጃፓንና ቻይና ፊደላት ያሉ (Logograms) ሲጠቀሙ ቆይተዋል። በመቀጠልም አንዳንድ ድምጽን ሊወክሉ የሚችሉ ምልክቶችን (Syllabic writing) ፈጥረዋል። በመጨረሻ ግን ሃሳባቸውን ሊገልፁ የሚችሉበት ፊደላት (alphabets) በመፍጠር ጥልቅ የሆኑ ሃሳቦችን እንኳ ሳይቀር ፊደላቱን በማገናኘት መግለጽ ችለዋል። በዚህም ፈጠራ አማካኝነት አንድ ፊደል አንድን ድምጽ እንዲወክል አድርገዋል። የእግሊዝኛው ፊደል ወይም “አልፋቤት” ከግሪኩ “አልፋ፣ ቤታ” ወይም ከፊኖሺያውኑና ከዕብራውያኑ “አሌፍ፣ ቤት” ከሚሉት የመጀመሪያ ሁለት ፊደላት ጥምረት የተጠፈረ ነው። ሰዎች መናገር የሚፈልጉትን፣ በአእምሯቸው ውስጥ ያለውን ሃሳብ ሌሎች እንዲገባቸው አድርገው በእነዚህ ፊደላት በመጠቀም ራሳቸውን መግለጽ መቻላቸው ስለለመድነው ምንም ላይመስለን ይችላል እንጂ እጅግ የሚያስገርም ክስተት ነው! (ግሪክና ዕብራይስጥ 22 ፊደላት፣ እንግሊዝኛ 26፣ አማርኛ ከ250 በላይ ቻይንኛና ጃፓንኛ ከ1800 በላይ ፊደላት እንዳሏቸው ይነገራል።)



Logograms ©Public Domain

**መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቋንቋ**

*መጽሐፍ ቅዱሳችን መጀመሪያ የተፃፈው በቻይንኛ ወይም በጃፓንኛ ፊደሎች ወይም ቋንቋ ሳይሆን በዕብራይስጥ፣ በአረማይክና በግሪክ ቋንቋ መሆኑንስ ያውቁ ኖሯል?*

የብሉይ ኪዳን ሰላሳ ዘጠኙም መፃህፍት ሁሉም በሚያስብል መልኩ የተፃፉት በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን የአዲስ ኪዳን ሃያ ሰባቱም መጻህፍት በግሪክኛ የተጻፉ ናቸው። ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ጥቂት የሚባሉ ጽሑፎች በአረማይክ ቋንቋ ተጽፈው ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ ትንቢተ ዳንኤል ከ2፡4 እስከ 7፡28፣ እዝራ 4፡8-16፣18 እና 7፡12-26 የተጻፉት በአረማይክ ነው። እስራኤላውያን ወደ ባቢሎን በምርኮ ከሄዱ በኋላ አረማይክ በዚያን ዘመኑ ፍልስጤም (ፓለስታይን) በሚገኙ ኗሪዎች መካከል የሚነገር ቋንቋ ስለነበር፣ አብዛኞቹ እስራኤላውያኖች ዕብራይስጥን ረስተው በአረማይክ ቋንቋ መጠቀም ጀመሩ። በዚህም ምክንያት በነህምያ 8፡8 እንደምናየው ሕዝቡ ቅዱሳት መፃህፍትን እንዲያስተውል ከእብራይስጥ ወደ አራማይክ ቋንቋ

ይተረጎሙላቸው ነበር። እንዲያውም ከእብራይስጥ ወደ አረማይክ የተተረጎሙ ጹሑፎች "ታርገም" በመባል ይታወቃሉ። ዕብራይስጥና አረማይክ አንድ አይነት ፊደላት የሚጠቀሙ ሲሆን አሁንም ጭምር በየመጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ ፊደሎቻቸውን እናገኛለን። ለምሳሌ በመዝሙር 119 በቁጥር 1፣9፣17 ወዘተ ማለት ከእያንዳንዱ 8 ቁጥሮች በኋላ እነዚህ የእብራይስጥ ወይም የአረማይክ ፊደሎች ከ"አሌፍ" እስከ መጨረሻው "ታው" የተባለው ፊደል ድረስ 22ቱንም ተጽፈው እናገኛቸዋለን። በሰቆቃው ኤርምያስ መጽሐፍ ውስጥም እነዚህኑ ፊደላት እናገኛለን። አንዳንድ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ይህ የሌላቸው ሊሆን ይችላል፣ አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ግን እነዚህ ፊደሎች ከነስሞቻቸው ይገኙባቸዋል።

### ያለ አናባቢ፣ ያለ ክፍተትና ያለ ስርዓተ-ነጥብ

የመጽሐፍ ቅዱስን አጻጻፍ በተመለከተ ሌላው አስገራሚ ነገር ደግሞ ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ በተፃፈበት ዘመን የዕብራውያን ፊደል ምንም አይነት አናባቢ (vowels) ሳይኖረው መፃፉ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን በቃላት መካከል ወይም በዓረፍተ ነገሮች መካከል ምንም አይነት ክፍት ቦታ ሳይኖር ግጥምጥም ብሎ (Scriptio continua or continuous script) መጻፉ ሌላው አስደናቂ ነገር ነው። ለምሳሌ ይህን አናባቢ የሌለውን በእንግሊዝኛ ፊደል የተፃፈ ጽሑፍ እንዴት ያነቡታል? "CMPTRNTWRK" ይህ እንግዲህ "computer network" ወይም "come Peter into work?" ሊሆን ይችላል። በተጨማሪ የዮሐንስ 3፡16ን በእንግሊዝኛ ቃላት መካከል ምንም ክፍት ቦታ ሳይኖር ፊደላቱ እንደተገጣጠሙ ለማንበብ እስኪ ይሞክሩ። FORGODSOLOVEDTHEWORLD HEGAVEHISONEANDONLYSONT HATWHOEVERBELIEVESINHIMS HALLNOTPERISHBUTHAVEETE RNALLIFE ለማመን ቢያስቸግርም የመጀመሪያው ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳናት የተጻፉት በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ቃላቱ ተገጣጥመው ያለአንዳች ክፍተት ነበር። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም ስርአተ ነጥብ አልነበራቸውም።



ክፍት ቦታ አልባ ግጥምጥም ጽሁፍ (Scriptio continua)
ምንጭ፡ God Incarnate

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ውስጥ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ በብዛት ይነጋገሩ የነበሩት በአረማይክ ቋንቋ ቢሆንም አዲስ ኪዳን የተፃፈው ግን በግሪክ ነው። ይህም የሆነው አብዛኛው ሕዝብ የሚገለገልበት ቋንቋ ግሪክ ስለነበር ነው። አልፎ አልፎ ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጥቂት የአረማይክ ቃላትን እናገኝበታለን። ስለዚህ ሃያ ሰባቱም የአዲስ ኪዳን መፃህፍት በግሪክ ቋንቋ የተፃፉ ናቸው። ይህ የሆነበት ምክንያት በወቅቱ አብዛኛው ሰው የሚግባባበት ቋንቋ ግሪክኛ በመሆኑ በዚያው እንዲያነበው መፃፍ ስለነበረበት ነው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሁፎች በምን ላይ ነበር የተጻፉት?

በጥንት ዘመን ጽሑፎች የሚፃፉት በድንጋይ፣ በሸክላ ጡቦች፣ ለመጻፊያ በተዘጋጀ ፓፒረስ፣ በተፋቁ የእንሰሳት ቆዳዎች ወይም ብራናዎች፣ በእንጨት፣ በዝሆን ጥርስ፣ በስብርባሪ ሸክላዎች፣ በብረት ዕቃዎች ላይ ነበር። በመጨረሻ በእኛ ዘመን በወረቀት ላይ ሆነ። የአፃፃፍ ሂደቱ ደግሞ አብዛኛው ሰው በጥቂቱም ቢሆን መፃፍ የሚችል ቢሆንም እንኳ አንዳንድ ደብዳቤዎች ወይም ጽሑፎች ግን የሚጻፉት ጥሩ መጻፍ በሚችሉ ፀሐፊዎች ነበር (በአገራችን የቁም ጸሃፊዎች የሚባሉትን ያስታውሷል)። አንዳንዶቹ መንደር ውስጥ የሚገኙ የግል ጸሐፊዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በክፍያ የሚሰሩ ጸሐፊዎች ነበሩ። በሌላ አነጋገር አንዳንዶቹ አማተር ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በክፍያ የሚሰሩ ፕሮፌሽናል ፀሐፊዎች ነበሩ ማለት ነው።



የ16ኛው ክ.ዘ. የግዕዝ ጽሑፍ

ጸሐፊዎቹ በፓፒረስ ላይ በሚጽፉበት ጊዜ በፖፒረሱ ላይ የሚገኙትን መስመሮች ለጽሑፎቻቸው በሚያመች መልኩ ወደ አግድሞሽ አዙረው ፓፒረሶቹ ላይ በሚገኘው ተፈጥሯዊ መስመር በመከተል ጽሑፎቻቸውን ሳያንጋድዱ ይጽፋሉ። በብራና ሲጠቀሙ ግን ቀለም ባልነካው ሹል ነገር ጽሑፎቻቸው እንዳይንጋደዱ የሚረዷቸውን አግድም መስመሮች ያሰምራሉ በተጨማሪም ሁለት ወይም ሦስት አምድና ኅዳግ (margin) ለመስራት የሚያመቹ መስመሮችን ጽሑፍ ከመጀመራቸው በፊት ያዘጋጃሉ።

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ይህ በዚህ ሁኔታ ቀጥሎ ዘመን እየተለወጠ ሲመጣ፣ እነዚህ ከፓፒረስ ለመፃፊያነት የተዘጋጁ ቅጠሎች እርስ በርሳቸው ተደራርበውና ታጥፈው ሲሰፉ፣ ከጥቅሉ (scroll) በተሻለ እንደ ዘመናችን መጽሐፍ በሚመስል መልክ ተዘጋጅተው ቀረቡ። በተጨማሪ ከፓፒረስ ተክል ከተዘጋጁት ጥንታዊ የመጽሐፍ ጥቅሎች ይልቅ፣በተመሳሳይ መንገድ ከእንሰሳት ቆዳ ተፍቆ በሚሰራ ብራና ላይ መፃፍ አመቺ ሆኖ ተገኘ። ይህም አዲስ ግኝት በቀላሉ ከቦታ ቦታ ለማዘዋወርና ለረጅም ዘመን ለማገልገል ስለሚያስችል ተፈላጊ ሆነ። ስለዚህ ከፓፒረስና ከብራና የተዘጋጁት እነዚህ መጽሐፍት፣ በተለያዩ ሰዎች የተጻፉ ጽሑፎችን በአንድ ጥራዝ ለማድረግ በማስቻላቸው ተወዳጅነትን አተረፉ። ስማቸውም "የተጠረዘ የጥንት ጽሁፍ" "codex" በመባል ታወቀ፣ የመጻሕፍት አዘገጃጀትም ከጥቅልል ወደ ጥራዝ ተቀየረ። በተለይ ከብራና የሚዘጋጀው የጥራዝ ጽሁፍ (ኮዴክስ) አዲስ ግኝት በቀላሉ ጹሑፍን በፊትና በጀርባው ለመፃፍ ከማስቻሉም በተጨማሪ ረዘም ያሉ ጽሑፎችን ለመጻፍ ስላስቻለ ተመራጭ እየሆነ መጣ። በዚህ የጥራዝ አሠራር መነሻነትም የወረቀት ጽሁፍና ጥራዝ መነሻ በማግኘት እስከዘመናችን ድረስ በአገልግሎት ላይ የዋለ መገልገያ ለመሆን ችሏል።

**ማስታወሻ፣** በዚህ በተከታታይ በምናወጣው ጽሁፍ የመጀመሪያ ክፍል በጥንት ጊዜ መልእክት እንዴት ይተላለፍ እንደነበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስሙን ከየት እንዳገኘ፣ የተጻፈበት ዓላማ ምን እንደሆነ፣ የተጻፈበት ቋንቋ ምን እንደሆነና በምን ላይ እንደተጻፈ ጠቅለል ያለ ሃሳብ ለመዳሰስ ሞክረናል። በቀጣዩ ክፍሎች መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እኛ ለሚያደርሰው መልዕክት የተጠቀመባቸውን አራት ተያያዥ ሒደቶችንና ሌሎች ጉዳዮችን እንመለከታለን።

ለዚህ ጽሁፍ በዋቢነት የሚከተሉትን መጻሕፍት ተጠቅመናል፣


Paul D. Wegner, *The Journey from Texts to Translations*, Grand Rapids, Michigan Baker Academic 2004.

Norman L. Geisler and William E. Nix, ***A General Introduction***

***to the Bible Revised and Expanded,*** Chicago, Ill. : Moody Press, ©1968

Bruce M. Metzger*, The Text of the New Testament, Its Transmission, Corruption, and Restoration*, New York, Oxford : Oxford UP, 1992.



# መጽሐፍ ቅዱስና ታሪኩ፡ መገለጥ! ክፍል ፪

ፓ/ር መስፍን ማንደፍሮ

በክፍል አንድ ዝግጅታችን መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው? በሚል ርዕስ በጥንት ዘመን መልዕክት እንዴት ይተላለፍ እንደነበር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስሙን ከየት እንዳገኘ፣ የተጻፈበት ዓላማና ቋንቋ ምን እንደነበር፣ ምን ዓይነት ስርዓተ ነጥብ ተጠቅሞ እንደነበር? መጀመሪያ በምን ላይ እንደተጻፈ? የመሳሰሉ ጥያቄዎች በማንሳት ጠቅለል ባለ መልኩ ለመዳሰስ ሞክረናል። በዚህ ክፍል 2 ጽሑፍ ደግሞ ጠለቅ ወዳለ ትንተና በመግባት ስለ መገለጥ እንማራለን።

ኖርማን ኤል ጊዝለር የተባሉ ምሁር በ“A General Introduction to the Bible” በተባለው መጽሐፋቸው፤ መፅሐፍ ቅዱስ ወደ እኛ ለሚያደርሰው መልዕክት አራት ተያያዥነት ያላቸው ሒደቶች እንዳሉ ይናገራሉ። እነርሱም **በመንፈስ አነሳሽነት መልዕክት በማምጣት ወይም በመንፈስ መመራት/በመገለጥ** (Inspiration/Revelation)፣ **በቀኖና** (Canonization)፣ **በስርጭት** (Transmission) እና **በትርጉም** (Translation) ሒደቶች ሲሆን፤ የእያንዳንዳቸው ትርጉም የሚከተለውን ይመስላል።

**በመገለጥና በመንፈስ ምሪት መልዕክት መቀበል** ወይም **በመንፈስ መመራት** ማለት እግዚአብሔር መልዕክቱን ለነቢያት በመንፈስ በመገለጥ እንዲመዘግቡት ያደረገበት ሂደት ሲሆን **ቀኖና** ማለት ደግሞ እነዚህ በነቢያት የተፃፉትን ጽሑፎች ማንነታቸው ወይም ምንነታቸው ፈትሾና ለይቶ እንደ ቅዱስ ጽሑፍ እውቅና አግኝተው ከያሉበት የተሰባሰቡበት ሂደት ነው። **ስርጭት** ወይም **ማስተላለፍ** የምንለው ደግሞ እነዚህ በእጅ የተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሌሎች እንዲያነቧቸውና ለትውልድ እንዲተላለፉ በመገልበጥ ወይም ኮፒ በማድረግ ቅጂዎቹን አባዝቶ ማስተላለፍ ሲሆን **ትርጉም** ማለት ደግሞ እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉበትን የመጀመሪያ ቋንቋ ለማያስተውሉ ሰዎች በቀጥታ በየቋንቋቸው እንዲያነቡና እንዲያስተውሉ ተርጉሞ ማቅረብ ነው።

በዚህ ጽሑፍ ትኩረት ሰጥተን የምንመለከተው ከላይ ከተዘረዘሩት ሂደቶች ውስጥ የመጀመሪያ የሆነውን መገለጥ (Revelation) የሚባለውን ነው። በአማርኛ መገለጥ ብለን የምንጠራው ጥሬ ቃል ትርጉም የተደበቀን መግለጥ፣ የተሰወረንና ድብቅ ሆኖ ያልተረዳነውን ነገር ማስረዳት ወይም መረዳት ማለት ነው። መገለጥ መለኮት ራሱን ለመግለጥ የሚያደርገው ድርጊት ነው። ይህም ድርጊት ነብዩን ከዚህ በፊት ስለአንድ ነገር ወይም ሁነት ሊያውቀው ወይም ሊረዳው የማይችለውን ነገር እንዲያስተውል የሚያደርግ ነው። በመገለጥ ውስጥ የሚደርሰን መረጃ ስለመለኮት ወይም ስለ ሌላ ነገር ሊሆን ይችላል። ሮጀር ኩን የተባሉ ምሁር መገለጥ ማለት "ከአምላክ ወደ ነብዩ የመጣው የመልዕክት ይዘት ነው" ይላሉ። ስለዚህ መገለጥ የሚያተኩረው የመልእክቱ ምንጭና ይዘት ላይ ነው።

ኃጢአት ወደዚህች ምድር ከገባ በኋላ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው የፊት ለፊት ግንኙነት ተቋረጠ (ዘፍ. 3፡9-12)፤ በዚህም ምክንያት ሰዎች በቀጥታ ከእግዚአብሔር መልዕክትን መቀበል የማይችሉበት ሁኔታ ተፈጠረ። ስለዚህ ከእግዚአብሔር መልዕክትን ወይም መገለጥን የሚቀበል ሰው ወይም ነቢይ እንዲኖር አስፈለገ። ይህ ነቢይ ብለን የምንጠራው ሰው እንደማንኛችንም ኃጢአተኛ ሰው ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔር መንፈስ ግን መልዕክት ይሰጠዋል፤ መልዕክቱንም ለሰዎች ሲያውጅም ሆነ በጽሑፍ ሲያስተላልፍ ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ አብሮት ይሠራል።

**መገለጥ ለምን አስፈለገ?**

መገለጥ ያስፈለገበት ቢያንስ ሶስት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። **የመጀመሪያው፤** የሰው የመረዳትና መርምሮ የማግኘት ወይም የማወቅ ውስንነት ነው። ይህም ወሰን የሌለውንና ከሰው ማስተዋል በላይ የሆነውን አምላክ ለመረዳትና መንገዱን ለማስተዋል መገለጥን አስፈላጊ ያደርገዋል።



**ሁለተኛው፤** እግዚአብሔር የግንኙነት አምላክ ከመሆኑ የተነሳና ራሱንም ለእኛ መግለጥ ስለሚፈለግ ነው።

**ሶስተኛው፤** ኃጢዓት በሰውና በአምላክ መካከል ያለውን መራራቅ ስላሰፋውና ሰዎችም ከውድቀት በፊት የነበራቸውን አምላክን የመረዳትና የማስተዋል ችሎታቸው በመንዳቱ ምክንያት ነው።

ስለዚህ ሰዎች በራሳቸው ጥረት ብቻ አምላክን ለማስተዋል ስለሚቸገሩ አምላክ በመንፈሱ ራሱን እንዲገልጥላቸው ያስፈልጋል ማለት ነው።

**መገለጥ**

አምላካችን እግዚአብሔር "በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና" (ዕብ. 1፡1) ከጥንት ጀምሮ ከሰው ልጆች ጋር ግንኙነት ሲያደርግ የኖረ አምላክ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ለሰው

ልጆች መልዕክትን ይገልጣል ወይም ይልካል። ከነዚህ የተለያዩ መንገዶች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፤ **በመላዕክት** (ዘፍ. 18)፣ **በሕልም** (ዳን. 7፡1፤ ዘኊ. 12፡6)፣ **በራእይ** (ኢሳ. 1፡1፤ ሕዝ. 1፡1፤ 8፡ 3)፣ **በተዓምር** (ዘጸ. 3፡2፤ መሳ. 6፡37፤ ዮናስ 4፡6)፣ **በተፈጥሮ** (መዝ. 19፡1)፣ **በድምጽ** (1 ሳሙ. 3፡4)፣ **በኅሊና ድምጽ** (ሮሜ 9:1-2፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የሚሉት አገላለጾች እንደ አስረጅ ሊወሰዱ ይችላሉ፤(ዘጸ. 5፡1፤ ኢሳ. 1፡24)፣ **በኡሪም ቱሚም** (ዘጸ. 28፡30፤ ዘኊ. 27፡21)፣ **ዕጣ በመጣል** (ምሳሌ 16፡33) እና **የሌሎችን ነቢያት ጽሑፍ ማጥናት** (ዳን. 9፡1-2) ናቸው። ይህን ከአምላክ የሚመጣ መገለጥ የስነመለኮት ምሁራን በሁለት ይከፍሉታል። እነርሱም **የወል (ጠቅላላ) መገለጥ** (General Revelation) እና **ልዩ (የተለየ) መገለጥ** (Special Revelation) በመባል ይታወቃሉ።

ጠቅላላ መገለጥ በመባል የሚታወቀው ለሁሉም ሰው፣ በሁሉም ጊዜና ቦታ ስለ እግዚአብሔር የሚያስረዱን ነገሮች ናቸው። የተለየ መገለጥ ብለን የምንረዳው ደግሞ ለተለዩ ሰዎች፣ በተለየ ጊዜና ቦታ የቀረቡ መልዕክቶች ናቸው። ጠቅላላ/የወል መገለጥ የተባለው በፍጥረት በኩል የተገለጸ ሲሆን ልዩ መገለጥ የተባለው ደግሞ በነቢያቱ በኩል የሚመጣ በጽሑፍ የሚተላለፍ መገለጥ ነው። ዛሬ ይህ ልዩ መገለጥ ወይም የጽሑፍ መልዕክት የሚገኘው በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ነው።




**ጠቅላላ ወይም የወል መገለጥ**

ጠቅላላ ወይም የወል መገለጥ የምንለው እግዚአብሔር በተፈጥሮ፣ በታሪክ ውስጥ እና በሰብዓዊ ይዘቶች ውስጥ ስለራሱ የገለጸልን ነው። በገሃዱ ዓለም ወይም በተፈጥሮ ወይም በፍጥረታት፣ በሰብዓዊ የማመዛዘን ሂደቶችና በደመነፍስ በኩል የምናገኘው መረዳት እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መንገድ ስለሆነ የወል (ጠቅላላ) መገለጥ በመባል ይታወቃል። ጠቅላላ መገለጥ የተባለበት ምክንያት ለማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ ተደራሽነት ያለው በመሆኑና የሚያስተላልፈውም መልእክት ጠቅለል ያለ ከመሆኑ የተነሳ ነው።

**በመጀመሪያ** የዚህን ጠቅላላ መገለጥ የምናስተውልበት ቦታ ተፈጥሮ ውስጥ ነው። በተለይ ስለ አምላክ በተፈጥሮ ውስጥ መገለጥን የሚያስረዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በመዝሙር 19፣ 1-4፤ በሐዋ. *ሥራ* 14፡17 ና በሮሜ 1፡ 20-21 ይገኛሉ።

ለምሳሌ ስለ አምላክ መኖር ከሚቀርቡት አስረጂ ነጥቦች መካከል አንዱ የሆነው ፈለካዊ ክርክር (cosmological argument) የሚባለው መከራከሪያ ነጥብ የአምላክን ኀልውና የምንገነዘበው በፍጥረታት ውስጥ በምንመለከተው ውበትና ልዩ ሞገስ ምክንያት ነው ይላል። መጽሐፍ ቅዱስም ለዚህ መከራከሪያ ነጥብ በሮሜ 1፡ 20-21ላይ እንዲህ ይላል።“የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ”።

ተፈጥሮ ላይ በመመርኮዝ የሚቀርበው ሌላኛው መከራከሪያ ነጥብ ደግሞ መነሾ-ፍጻሜ ክርክር (teleological argument) የተባለው ሲሆን ስለ እግዚአብሔር ኀልውና ያስረዳል ብሎ

የሚያቀርበው ነጥብ በፍጥረታት ውስጥ የምንመለከተውን የተለያየ ንድፍ ወይም ዲዛይን፣ ሞድ (ሁኔታ) እና ስርዓት አስደናቂነት ከዓላማው ወይም ከመጨረሻው ተነስቶ በማሳየት ነው። እነዚህ ነገሮች ስለ አምላክ መኖርና ፈጣሪነት የሚያስረዱ፤ የሚመሰክሩና የሚናገሩ ናቸው።

**ሁለተኛው** ጠቅላላ መገለጥን የምናገኝበት ቦታ ደግሞ በታሪክ ውስጥ ሲሆን ይህም እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የፈጸመውንና እየፈጸመ ያለውን በቅርበት በመመልከት ልንረዳ የምንችለው ነው (ዳን. 2:24-49)።

**በሶስተኛ** ደረጃ ጠቅላላ መገለጥን የምንገነዘበው የሰውን ልጅ አካላዊና አእምሮአዊ ችሎታዎችን በመመልከት ሲሆን የሰው ሞራላዊ የሆነ ተፈጥሮአዊ ይዘቱ፣ ክፉንና ደጉን ለማመዛዘንና ለመምረጥ መቻሉ፣ በተጨማሪም ለመንፈሳዊ ጉዳይ ያለው ከፍተኛ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ስለ ፈጣሪ አምላክ የሚገልጠው ነገር ነው (ዘፍ. 1:26፣27)።

እንግዲህ ይህ የወል (ጠቅላላ) መገለጥ ስለ እግዚአብሔር መኖር ብቻ የሚያስረዳ ሳይሆን እንዲያውም ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት፣ የመፍጠር ችሎታ፣ ውበትን መውደድ፣ የጥበቡን



ጥልቅነት፣ ሚዛን የጠበቀ መሆንና ድንቅነቱን ያሳያል። በተጨማሪ ጠቅላላ መገለጥ ሰው ሁሉ የተወሰነ ነገር ስለ አምላክ የሚያውቀው እንዲኖረውና ሰዎች ሁሉ የራሳቸው የሃይማኖት ዝንባሌ ወይም አስተሳሰብ እንዲያዳብሩ አስተዋጽዖ አድርጓል። ታዲያ ይህ የወል መገለጥ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጀርባ መኖሩን ከማስረዳት ውጪ ብዙ የሚሰጠን ተጨማሪ ምሪት ባለመኖሩ ምክንያት የበለጠ ስለ አምላክ በጥልቀት ለመረዳት ልዩ የሆነ መገለጥ አስፈልጎናል።

**የተለየ መገለጥ**

ከላይ ስለ ልዩ መገለጥ የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ መገለጥ የምንለው በቀጥታ አምላክ ራሱን ገልጦልን የምንረዳበት ወይም የምናስተውልበት መንገድ ነው። ይህም በራዕይ፣ በህልምና በድምጽ ነቢያት የተቀበሉትን ምሪት በጽሑፍ ለእኛ በማስተላለፋቸው ምክንያት ያገኘነው ነው (መዝ. 19:7-14፣ ዕብ. 1:1-3)።

እንግዲህ በልዩ መገለጥ በኩል ካልሆነ በስተቀር ስለ እግዚአብሔር ልንገነዘባቸው የማንችላቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ኅብረት ሊኖረው እንደሚፈልግ ወይም መድኃኒዓለምን በማመን ስለሚገኘው መዳን መረዳት የምንችለው በዚህ ልዩ መገለጥ በኩል ካልሆነ ፍጥረትን በመመልከት ብቻ መረዳት የሚቻል አይደለም። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ እግዚአብሔር የሚያስረዳን ልዩ መገለጣችን እና ዋና ወይም ቀዳሚ ምንጫችን ነው። ለዚህ ደግሞ 2ኛ ጢሞ. 3:16-17፣ 2ኛ ጴጥ. 1:20-21 ደጋፊ መረጃ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ።

ይህ የተለየ መገለጥ የራሱ የሆኑ ባህሪያት አሉት። ከነዚህ ባህሪያት መካከል አንደኛው የግል ልምምድ ሲሆን እግዚአብሔር ለግለሰብ ወይም ለሕዝብ ራሱን በስሙ ሲያስተዋውቅ ወይም ቃልኪዳን ሲገባ በታየው ልምምድ ላይ የተገለጸ ባህርይ ነው። ሁለተኛው የተለየ መገለጥ ባህርይ ደግሞ ሰብዓዊ ፍጥረት ሊረዳው በሚችልበት ቋንቋና ደረጃ የተገለጠ መሆኑ ነው። በመለኮታዊ ቋንቋ የተገለጠ ቢሆን ኖሮ ሰዎች ሁሉ ሊያስተውሉት ባለመቻላቸው ምክንያት ይቸገሩ እንደነበር ለሁላችንም ግልጽ ነው። በመጨረሻም በዚህ ልዩ መገለጥ ውስጥ ከምንመለከታቸው ባህርያት መካከል የምናስተውለው ነገር ንጽጽራዊ መሆኑን ነው። ከሰብዓዊው ዓለም የተወሰዱ ነገሮችን በማነጻጸር ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን እንዲያስተውሉ ለማድረግ ይሞክራል። ለምሳሌ ስለፍቅር ስንነጋገር የአምላክ ፍቅር ደረጃው እጅግ ከፍ ያለ ቢሆንም እንኳ ከእናትና አባት ፍቅር ጋር በማነጻጸሩ ምክንያት ለእኛ ይህንን ፍቅር ለመረዳት እጅግ ያቀልልናል። (ኢሳ. 49፡15) "እናት የምታጠባውን ልጇን ልትረሳ ትችላለችን? ለወለደችውስ ልጅ አትራራለትምን? ምናልባት እርሷ ትረሳ ይሆናል፣ እኔ ግን እልረሳሽም"።




በተጨማሪ ይህ የተለየ መገለጥ ወደ ሰዎች ልጆች የደረሰበት ሶስት የተለያዩ መንገዶች (ሞዳሊቲዎች) አሉ። እነርሱም በ***ታሪካዊ ሁነቶች***፣ **በመለኮታዊ ንግግሮች**ና **በአምላክ *ሥጋ* መልበስ (*ምሥጢረ ሥጋዌ*)** በኩል የተገለጹት ልዩ መገለጦች ናቸው።

በ***ታሪካዊ ሁነቶች*** በኩል የተገለጸው ይህ ልዩ መገለጥ ለምሳሌ በሚከተሉት የታሪክ ይዘቶች በኩል ተብራርቷል። የአብርሃም እንዴት እንደተጠራ፣ በዮሴፍ ዘመን እግዚአብሔር ሰዎችን እንዴት ከረሃብ እንደታደገ፣ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ እንዴት ከባርነት ቀንበር ነጻ እንዳወጣቸው፣ የተስፋይቱን ምድር እንዴት እንዳወረሳቸው፣ ተመልሰው ወደ ምርኮ አገር መወሰዳቸውና ከምርኮ ነጻ ወጥተው ወደ አገራቸው መመለሳቸው፣ የክርስቶስ ኢየሱስ መወለድ፣ መኖር፣ መሞትና ከሞት መነሳት፣ ወደ ሰማይ ማረግ፣ የቤተክርስቲያን በዚህ ምድር መኖርና መስፋፋት፤ ወዘተ እነዚህ ሁሉ በታሪካዊ ይዘቶች ውስጥ ልዩ መገለጥ የተላለፈበት አንደኛው መንገድ ነው።

***ሁለተኛው*** ደግሞ ***መለኮታዊ ንግግር*** የምንለው ነው። ለምሳሌ "የእግዚአብሔር ቃል እንደዚህ ሲል ወደ እኔ መጣ"፣ ወይም "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" በሚሉት አገላለጾች የተዘረዘሩ ሃሳቦች በዚህ ሥር የሚካተቱ ናቸው (ኤር. 1፡18፣ ሕዝ. 12፡ 1፣8፣17፣21፣26፤ሆሴዕ 1፡1 ኢዩኤል 1፡1 አሞጽ 3፡1 ይመልከቱ)። አምላክ በዚህ መለኮታዊ ንግግሩ ስለራሱ ይናገራል፤ ዕቅዱን ያሳውቀናል፤ ፈቃዱን ይነግረናል። ይህ ልዩ መገለጥም በሚሰማ ድምጽ፣ በጸጥታ ውስጥ፣ በህልም፣ በራእይና በመሳሰሉት መንገዶች መልዕክቱ ለነቢያት ደርሷል።

***በመጨረሻም*** ይህ ልዩ መገለጥ የመጣው በዚህ ምድር ላይ በልጁ በኢየሱስ **ክርስቶስ *ሥጋ* መልበስ (*ምሥጢረ ሥጋዌ*)** አማካኝነት ነው። ይህ ደማቁና ከፍ ያለው መገለጥ ነበር። ኢየሱስ በተናገረበት ጊዜ አምላክ ራሱ ነበር የተናገረው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ከፍተኛውና ሙሉው መገለጥ ነበር። ዕብራውያን 1፡1-2 እንደዚህ ይለናል፤ "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን" (በተጨማሪ የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከቱ ዮሐ. 14፡9፤ 1ኛ ዮሐ. 1-2)።

እንግዲህ መገለጥ የብርሃን መምጣትን የሚያስታውሰን ነው። ብርሃን ደግሞ በባሕርይው በጨለማ ውስጥ የተደበቀን ይገልጣል፣ ጨለማን ያባርራል፣ ብርሃን ሲሰፍን ጨለማ ቦታ አይኖረውም። በብርሃን ኃይል ማየት እንችላለን፤ መጽሐፍ ቅዱሳችን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ብርሃናችንና ታላቁ መገለጣችን ነው (መዝሙር 119፡105)፤ ስለዚህ ለዚህ መገለጥ ክብር በመስጠት እናንብበው ምክሩንም በመከተል እንታዘዝ። “እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ ድነት ችላ ብንል እንዴት ልናመልጥ እንችላለን?” (ዕብ 2፡3)

**ዋቢ መጻሕፍት**

Coon, W. Roger. “Inspiration/Revelation: What It Is and How It Works. Part I: The Prophetic Gift in Operation.” The Journal of Adventist Education.Vol 44, No. 1 October-November, 1981.

Geisler, Norman L. and William E. Nix, *A General Introductionto the Bible Revised and Expanded.* Chicago, Ill.: Moody Press, 1968

Reid, George W. ed. *Understanding Scripture: An Adventist Approach.* Biblical Research Institute, Silver Spring: Review Herald, 2005.

Song, Ho Kyung. *Revelation, Inspiration, and Prophetic Guidance.* Adventist International Institute of Advanced Studies, n.d.

Wegner, Paul D. *The Journey from Texts to Translations.* Grand Rapids, Michigan Baker Academic 2004.

## ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት ገራሚ ነጥቦች፤

- መሉው መጽሐፍ ቅዱስ ከ532 ቋንቋዎች በላይ ሲታተም፤ በከፊል (አዲስ ኪዳን) በ2883 ቋንቋዎች ታትሟል።
- መጽሐፍ ቅዱስ የአንድ ሰው ውጤት ሳይሆን የበርካታ ጸሐፍት ስብስብ ነው፤ እነዚህም እረኞችን፣ ነገሥታትን፣ ገበሬዎችን፣ ካህናትን፣ ገጣሚዎችን፣ አሣ አጥማጆችን፣ ወዘተ ያካተተ ነው።
- ብሉይ ኪዳንን ለመጻፍ 1000 ዓመታትን ሲወስድ አዲስ ኪዳን ግን ከ50 – 75 ባሉት ዓመታት ውስጥ ተጠናቅቋል።
- በግምት በየዓመቱ 100 ሚሊዮን ቅጂዎች ይሸጣል።
- ረጅሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ መዝሙር 119 ነው፤ 176 ቁጥሮች አሉት። አጭሩ ደግሞ መዝሙር 117 ነው፤ ቁጥሮቹም ሁለት ብቻ ናቸው።
- መጽሐፍ ቅዱስን ከላቲን ወደ እንግሊዝኛ ለመጀመሪያ ጊዜ የተረጎመው **ጆን ዊክሊፍ** (1320 - 1384) ነው። በወቅቱ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይነበብ ገዝታ የነበረችው የሮም ካቶሊክ ቤ/ክ ይህንን የትርጉም ሥራ በመሥራቱ መቀጣጫ ይሆን ዘንድ ጆን ዊክሊፍ ከሞተ በኋላ (በ1428 አካባቢ) አስከሬኑን አስቆፍራ አውጥታ አቃጥላዋለች።
- የመጀመሪያውን አዲስ ኪዳን ያተመው **ዊሊያም ቲንደል** (1494 – 1536) ሲሆን እርሱም ሥራው እንደ ጥፋት ተቆጥሮበት በመጀመሪያ በማነቅ ከተገደለ በኋላ በእሳት ተቃጥሏል።
- በ2016 በተደረገ የዳሰሳ ጥናት፤ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች፣ ከወጣቶች ይልቅ አረጋውያን፣ ከነጮችና ሌሎች ዘሮች ይልቅ ጥቁሮች መጽሐፍ ቅዱስን ያነባሉ።
- በኢትዮጵያ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ኦሮሚኛ የተረጎሙት **ኦናሲሞስ ነሲብ** ናቸው (እኤአ 1856 – 1931)። ይህንን በማድረጋቸው ለስደት የተዳረጉት ኦናሲሞስ፤ ሲወለዱ ስማቸው ሒካ ይባል የነበረ ሲሆን ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ ኦናሲሞስ የሚለውን ስም ወስደዋል። ከእርሳቸው በፊት ሩፎ የተባሉ አስፈላጊ የሚባሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ወደ ኦሮሚኛ ተርጉመዋል።

# መጽሐፍ ቅዱስና ታሪኩ (ክፍል ፫)፡

# የመንፈስ ምሪት የወለደው መጽሐፍ

ፓ/ር መስፍን ማንደፍሮ

"በጌታ ቀን **በመንፈስ ነበርሁ፥** በኋላዬም የመለከትን ድምፅ የሚመስል ታላቅ **ድምፅ ሰማሁ፥** የምታየውን በመጽሐፍ ጽፈህ ... ላክ **አለኝ**" (ራዕይ 1፡10-11)። "እግዚአብሔርም በጎቹን ከመከተል **ወሰደኝ፥** እግዚአብሔርም፡- **ሂድ፥** ለሕዝቤም ለእስራኤል ትንቢት **ተናገር አለኝ**" (አሞጽ 7፡15)። "እግዚአብሔር **እንዲህ ይላል**፡- ያገለግሉኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ" (ዘጸ 9፡1)። "**የእግዚአብሔርም ቃል** ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፡-" (ሕዝ 21፡8)። "**የቃሉንም ድምፅ ሰማሁ** የቃሉንም ድምፅ በሰማሁ ጊዜ ደንግጬ በምድር ላይ በግምባሬ ተደፋሁ"(ዳን 10፡9)። "**ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ፤**" (አሞጽ 7፡1)። እነዚህን የመሳሰሉ አገላለጾች ነቢያት በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተገለጠላቸውን መልዕክት እንደመዘገቡልን የሚያስታውሱ ናቸው። በዚህ ክፍል ሦስት ጽሑፍ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጻፍ ስላደረገው ስለ መንፈስ ምሪት በጥቂቱ እንነጋገራለን። በቀዳሚዎቹ የክፍል አንድና ሁለት ዝግጅታችን መጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው? እንዴት ተጻፈ? ስሙን ከየት አገኘ? መገለጥ ምንድነው? ወዘተ በሚሉ ርዕሶች ላይ ሰፊ ትንታኔ ሰጥተን ነበር።



መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት የመንፈስ ምሪት (Inspiration) አምላክ ለነቢያት ስብዕናቸውንና ማንነታቸውን ሳይጋፋ መለኮታዊ ሥልጣን ያለው ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ ያደረገበት ምሥጢራዊ አሠራር ነው። የዚህ አሠራር ሒደት ውጤት መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ምንጭ መሆኑን ሲያስረዳ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ በእነዚህ መጻሕፍት መልእክት ውስጥ እንደሚገኝ ይጠቁመናል። መንፈስ ቅዱስ ነብዩ የተቀበለውን መልእክት እንዲያስተውልና በታመነ መንገድ ለሌሎች እንዲያስተላልፍ አቅም ይሆነዋል። ሮጀርስ ኩን የተባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር ሲናገሩ በመንፈስ መመራት ማለት "በተለየ መንገድ አንድ ወንድ ወይም ሴት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን መልእክት ተቀብለው፤ መልዕክቱን ሳያዛቡ፣ በትክክልና በሚያስተማምን መልኩ የማስተላለፍ ሒደት ነው" ይላሉ። እንግዲህ ከዚህ በፊት እንዳጠናነው መገለጥ የሚያተኩረው የመልእክቱ ምንጭና መሰጠት ላይ ሲሆን የመንፈስ ምሪት የሚያተኩረው ደግሞ መልእክቱ እንዴት እንደመጣና አመዘጋገቡ ላይ ነው።

እንግዲህ ዘፍ. 3፡8ን መሠረት በማድረግ ከውድቀት በፊት አዳምና ሔዋን ከፈጣሪያቸው ጋር የተቀራረበ የፊት ለፊት ግንኙነት እንደነበራቸው መረዳት ይቻላል። ሆኖም ኃጢአት ከሠሩ በኋላ ይህ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው መልካም ግንኙነት መበላሸቱን እንዳወቁ በተሰማቸው ፍርሃት፣ ባደረጉት መደበቅና መሸሸግ በግልጽ ታይቷል። በአዳምና ሔዋን ኃጢያት ምክንያት የሰው ልጆች በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን የፊት ለፊት ግንኙነት በመቋረጡ፤ እግዚአብሔር በተለየ መገለጥ አማካኝነት ለተለዩ ሰዎች በተለየ ጊዜና ቦታ ራሱን በመግለጥ ከእርሱ ጋር የነበረንን የግንኙነት ክፍተት አጥብቦታል።

ስለዚህ ከእግዚአብሔር መልእክት ወይም መገለጥን የሚቀበል ሰው ነብይ ተብሎ ሲታወቅ፤ እርሱም/ሷም እንደማንኛችንም ኃጢአተኛ ሰው ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔር መንፈስ መልእክት ይሰጠዋል። መልዕክቱንም ለሰዎች በንግግር ሲያውጅም ሆነ በጽሑፍ ሲያስተላልፍ የእግዚአብሔር መንፈስ አብሮት ይሠራል። ይህ ዓይነቱ የመንፈስ ቅዱስ አሰራር በእንግሊዝኛ "Inspiration" ሲባል በአማርኛ ትክክለኛ

ትርጉሙን መስጠት ቢያስቸግርም በመንፈስ ምሪት መልዕክት ተቀብሎ ማስተላለፍ ብለን ልንጠራው እንችላለን። ነቢያትም የተቀበሉትን መገለጥ በመጻሕፍት ላይ አስፍረው ለትውልድ ሁሉ እንዲተላለፍ አድርገዋል። በመሆኑም ይህ ታላቅና በመንፈስ ምሪት የተወለደው መጽሐፍ፤ በዘመናችን መጽሐፍ ቅዱስ በመባል ይታወቃል።

ቅዱሳት መጽሕፍትን የጻፉት ነብያት ከተለያየ የሕይወት ተሞክሮ የመጡ ናቸው። አንዳንዶቹ እንደ አሞጽ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ፣ እንደ ኤርምያስና ሕዝቅኤል በክህነት የሚያገለግሉ፣ እንደ ዳንኤል በከፍተኛ የመንግሥት ዕርከን ላይ የነበሩ፣ እንደ ጴጥሮስና ዮሐንስ በዓሣ አጥማጅነት የሚተዳደሩ፣ እንደ ኢሳይያስና ሚክያስ ለነብይነት የተጠሩ፣ እንደ ሉቃስ ሐኪም የነበሩና እንደ ማቴዎስ በግብር (ቀረጥ) ሰብሳቢነትና በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ ነበሩ።

መጻሕፍቱ የተጻፉበት አገራት በእስራኤል፣ በባቢሎን፣ በግሪክ፣ በጣልያንና በመሳሰሉት የጂኦግራፊያዊ ክልል ውስጥ ሲሆን በውስጣቸው የያዙት የሥነጽሑፍ ይዘት ደግሞ እንደ ታሪክ፣ ሕግ፣ ግጥም፣ ምሳሌ (ጥበባዊ



አገላለጽ)፣ ወንጌል፣ ደብዳቤ ያሉ ናቸው። ለምሳሌ የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻህፍት (ዘፍጥረት፣ ዘጸዓት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኊልቅ እና ዘዳግም) ሕግ ወይም ኦሪት በሚባለው ሲካተቱ መጽሐፈ ኢዮብ፣ መዝሙራተ ዳዊት፣ መጽሐፈ ምሳሌ፣ መክብብ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን በሥነግጥም ስልት የተጻፉ የጥበብ መጻሕፍት ናቸው። ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አምላክ የሚናገሩ ከተለያየ ቦታ የተሰባሰቡ ስነ-ጽሑፎች ውጤት ብቻ ሳይሆን በውስጡ ልዩና አስደናቂ የሆነ፣ የማይጣረስ የዓላማና የሃሳብ አንድነት የሚገኝበት መጽሐፍ ነው። ለዚህም አስገራሚ የሃሳብ አንድነት ምክንያት ሁሉም መጻህፍት ሲጻፉ የመራው አንድ መንፈስ በመሆኑ ነው።

በመንፈስ ምሪት መልዕክት የመቀበል ዓላማ ነብዩ መልእክት ሲቀበልና ሲያውጅ ከስህተት የጸዳ እንዲሆን ማድረግ ነው። ስለዚህ መልዕክትን በመንፈስ ምሪት የመቀበል ዋነኛው ነገር ከእግዚአብሔር የተላከው መልእክት ሳይበረዝና ሳይደለዝ መጠበቁና ለሰዎች መድረሱ ነው። ታዲያ በነብዩ የሚተላለፈው መልእክት መጀመሪያ በእግዚአብሔር ሃሳብ ውስጥ የነበረ መሆኑን ልብ ይሏል።

ይህ የተለየ መገለጥ በመባል የሚታወቀው መጽሐፍ ቅዱሳችን ብሉይና አዲስ በመባል በሁለት ታላላቅ ኪዳኖች ይከፈላል። ብሉይ ኪዳን ከሙሴ ዘመን 1450 ዓዓ (ዓመተ ዓለም) ጀምሮ እስከ 400 ዓዓ ድረስ ተጽፎ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ አዲስ ኪዳን ደግሞ ከ40-100 ዓም ድረስ የተፃፈ ነው። እነዚህ የብሉይና የአዲስ ኪዳን 66 መጻሕፍት ወደ 40 በሚጠጉ ሰዎች የተፃፉ ሲሆኑ ለመፃፍ የወሰዱት አጠቃላይ ጊዜ ወደ 1500 ዓመታት የሚያክል ነው።

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስክርነት**

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ምሪት መጻፉን ራሱ ይመሰክርልናል፤ ይህንንም የሚገልጹ ሁለት ጥቅሶችን አሉ። የመጀመሪያው ጥቅስ እንዲህ ይላል፤ **“ቅዱሳን መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው”** (2ኛ ጢሞ.3፡16-17 አዲሱ መደበኛ ትርጉም (አ.መ.ት.))። ይህ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ “የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው” በማለት የተገለፀው

አባባል የግሪኩ “ቲዮፕኒዩስቶስ” የሚለውን ቃል ነው። ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ የሚገኝ ሲሆን ከሁለት የግሪክ ቃላት ውህደት የተፈጠረ ነው። እነርሱም “ቲዮ” እና “ፕኒዩማ” ሲሆኑ ትርጉማቸውም እንደ ቅደም ተከተላቸው “አምላክ” ማለትና “መንፈስ” ወይም “እስትንፋስ” ማለት ነው። ቃላቱ ሲዋሐዱ የሚሰጡት ትርጉም ግን “የእግዚአብሔር እስትንፋስ” ወደ ህልውና ያመጣቸው የሚለውን ስሜት ነው። ይህ ማለት ልክ አዳም በአምላክ እስትንፋስ ወደ ኅልውና እንደመጣና (ዘፍ.2፡7) በተመሳሳይ መልኩ ዳዊት “በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ” (መዝ.33፡6) እንደሚለው ቅዱሳን መጻሕፍትም ወደ ኅልውና የመጡት በእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው የሚል ትርጉም ያዘለ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ የሰጠው ሁለተኛ ምስክርነት በ2ኛ ጴጥ 1፡21 ላይ የሚገኝ ነው። ጥቅሱም እንደዚህ ይላል **“ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም”** (አ.መ.ት.)። በአማርኛ “ተመርተው” (የ1962 ዓም ትርጉም ደግሞ “ተነድተው”) የሚለው ቃል የግሪኩ “ፌሮሜኖይ” ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። በርግጥም “ፌሮ” ማለት መሸከም፣ ማንቀሳቀስ፣ መምራት፣ መንዳት፣ ማምጣት የሚሉ ትርጉሞችን የያዘ ነው። ስለዚህ የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ቃሉን “በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው” በማለት በትክክል ተርጉመውታል። ይህ ቃል በሐዋርያት ሥራ 27፡15 ላይ በተመሳሳይ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። **“መርከቢቱ በማዕበሉ ስለተያዘች ወደ ነፋሱ ልትገፋ አልቻለችም፤ ስለዚህ … ለቀን በንፋሱ ተነዳን (ኢፌሮሜታ) …”** (አ.መ.ት.) እንግዲህ ንፋሱ መርከቢቱን ወደ ራሱ አቅጣጫ እንደነዳት ሁሉ መንፈስ ቅዱስም “ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች”ን ወይም ነቢያቱን ጽሑፋቸውን በሚጽፉበት ጊዜ ወደራሱ አቅጣጫ መርቷቸዋል። ስለዚህ ቅዱሳን መጻሕፍት የነብያት በመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ ሥር መሆን የወለዳቸው ነው። በዚህ መሰረት ጴጥሮስ እንደተናገረው ትንቢት ወይም ቅዱሳን መጻሕፍት ምንጫቸው ሰብዓዊ ሳይሆን መለኮታዊ ነው። ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቆስቋሽነት ወይም ምሪት የጻፏቸው እንጂ ከሰብዓዊ ምንጭ አልተቀዱም።



ስለዚህ በጢሞቴዎስ እና በጴጥሮስ ላይ የተገለጸውን ሃሳብ ስናጠቃልል “ቲዮፕኒዩስቶስ” የሚለው የግሪክ ቃል የእግዚአብሔር እስትንፋስ (መንፈስ) የፈጠራቸው መጻሕፍት መኖራቸውን ሲገልጽ “ፌሮሜኖይ” የሚለው ቃል ደግሞ የመንፈስ ተፅዕኖ (ምሪት) በፀሐፊዎቹ (በነብያቱ) ላይ አርፎ እንደነበር የሚያስረዳ ነው። ይህ ሃሳብ በእንግሊዝኛ “ኢንስፓይሬሽን” ስንለው በአማርኛ “የመንፈስ ምሪት የወለዳቸው” የሚል ትርጉም ብንሰጠው ገጣሚ ይመስለኛል።

ከላይ የተመለከትናቸው ሁለት ጥቅሶች፤ ቅዱሳን መጻሕፍት በመለኮትና ሰብዓዊ ተሳትፎ የተጻፉ መሆናቸውን ቢናገሩም እነዚህ መለኮታዊና ሰብዓዊ ወኪሎች በእንዴት ዓይነት መንገድ ወደ ኅብረት መጥተው መገለጡ እንዲፈጸም እንዳስቻሉ ግን አያስረዱም። በዚህ ምክንያት የስነመለኮት ተመራማሪዎች የተለያየ የኢንስፓይሬሽን ንድፈ ሃሳቦችን (ቲዎሪዎችን) ያቀርባሉ። ሆኖም ግን እነዚህን ንድፈ ሃሳቦች በዝርዝር ለመመልከት ከዚህ ጽሑፍ ዓላማ ውጪ ስለሆነ ወደዚህ ሐሳብ ዳሰሳ ውስጥ አንገባም።

በመጨረሻም በነዚህ ሁለት ጥቅሶች (1ኛ ጢሞ.3፡15 እና 2ኛ ጴጥ.1፡21) ላይ በመመስረት ቢያንስ ወደ ሁለት ዋና ድምዳሜዎች ላይ ለመድረስ እንችላለን። እነርሱም አንደኛው እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ምንጭ

መሆኑን ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የላከው መልእክት መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ምንና ማንን ማመን እንዳለብን የሚነግረን፤ በተጨማሪም እንዴት ሕይወታችንን መኖርና መምራት እንዳለብን የሚያሳስበን ታላቁ ሰበር ባለሥልጣን ነው።

**ዋቢ መጻሐፍት**


Coon, W. Roger. "Inspiration/Revelation: What It Is and How It Works. Part I: The Prophetic Gift in Operation." *The Journal of Adventist Education.* Vol 44, No. 1 October-November, 1981.

Geisler, Norman L. and William E. Nix, *A General Introduction to the Bible Revised and Expanded*. Chicago, Ill.: Moody Press, 1968.

Reid, George W. ed. *Understanding Scripture: An Adventist Approach*. Biblical Research Institute, Silver Spring: Review Herald, 2005.

Song, Ho Kyung. *Revelation, Inspiration, and Prophetic Guidance*. Adventist International Institute of Advanced Studies, n.d.

Wegner, Paul D. *The Journey from Texts to Translations.* Grand Rapids, Michigan Baker Academic 2004.